PANORAMA # XVI

# የትዝብት አድማስ

የካቲት 28 2000 ዓም

## <u>እየሞቱ መኖር፤ እየኖሩ መሞት</u>

ደራሲ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው÷ ከዛሬ ግማሽ ምዕተ ዓመት በፊት ለጻፉት መጽሐፋቸው÷የሰጡት ርዕስ÷ <u>አልሞትኩም ብየ አልዋሽም</u> የሚል እንደ ነበር የዕድሜ ባለፀጋ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስታውሰው ነው:: የመጽሐፉ ዋነኛ ባለታሪክ÷ አቶ ተማቹ÷ሳይሞት እንደ ሞተ ተቆጥሮ÷ ሰብዕናውን÷ ሚስቱንና ልጆቹን÷ ቤቱንና ንብረቱን÷ ክብሩንና ማዕረጉን በገዛ ሀገሩ÷ በአንድ የኢጣሊያ ወራሪ የጦር መኮንን በመነጠቁ ምክንያት÷ ጥቃቱንና ስቆቃውን ለመግለጽ የተጻፈ ታሪክ ነበር:: ይህ ታሪካዊ ልብ ወለድ መጽሐፍ በጊዜው የመላውን አንባብያን አድናቆትና አክብሮት እንዳገኘ የሁሉም ትዝታ እንደነበር÷ መጽሀፉን እያነበበ ለአደገው ትውልድ የማይረሳ ቅርስ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: ባለ ታሪኩ አቶ ተማቹ÷ ውርደቱን ተቀብሎ መኖሩ ስለ ከበደው÷ በቁሙ መሞቱን ተረድቶ÷ ከእንግዲህስ ወዲያ÷ "<u>አልሞትኩም ብየ አልዋሽም</u>" የሚለውን ንግግር የሕይወቱ ማሳረጊያ አድርጎታል::

ይህ የዛሬው አሳረኛ ትውልድ÷ እንዳለመታደል ሆኖበት ልክ የአቶ ተማቹን ዓይነት ዕድል ገጥሞት÷ እየሞተ የሚኖርና እየኖረ የሚሞት መሆኑን እየተገነዘበው አይደለም ለማለት ባይቻልም÷ የሁኔታውን ክብደትና ጥልቀት ግን የቱን ያህል በስፋት እንደሚከታተለው በዕርግጠኝነት ማወቅ አይቻልም:: ምናልባት ነገ ሀገሪቱን የሚረከባት ይህ ትውልድ ይህንን እየሞቱ የመኖሩንና እየኖሩ የመሞቱን ሁኔታና ሂደት በሚገባ ተረድቶት÷ በጊዜው ሀገራዊ መፍትሄ ለማግኘት ካልተጣጣረ÷ ከአባቶቹና እናቶቹ የወረሰውን ሀገር አኩሪ ታሪክና ባሕል÷ እሴትና እምነት ቀስ በቀስ በሂደት እያጣ ይሄድና÷ ሀገሪቱን ነገ ሌላ÷ ፍፅም ሌላ የሆነ ትውልድ እንደሚረከባት ስጋታቸውን የሚገልጹ ታዛቢዎች ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: የስድሳ ስድስቱን አብዮታዊ ትውልድ ያፈራችው ኢትዮጵያና አሁን በመጠራሞት ላይ ያለችው ኢትዮጵያን በበርካታ መስፈርቶች ስትገመገም÷ የአሁኑ ትውልድ ምን ያህል የኢትዮጵያን መሠረታዊ ማንነት ለማወቅ እንደተነፈገው መገመት ከባድ አይሆንም::

ይህንን ክስተት በሚገባ ለመረዳትና በሚዛናዊ መስፈርት ለመገምገም የሚቻለው፤ ቢያንስ ለአለፉት ስድሳና ሰባ ዓመታት ክልል ሂደት የተጓዘውን ትውልድ ከተፈራረቁበት ሦስት ሥርዓቶች አኳያ ለማየት ሲሞከር

ይመስለናል። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማብቂያና የኢጣሊያ ፋሽስት ወራሪ ጦር ከሀገራችን ከተባረረ በኋላ ጀምሮ እስከ ዛሬ ሀገራችን የተጓዘችበትን ሂደት፤ እንዲሁም የተለዋወጠውን ትውልድና ሁኔታ፥ የተፈራረቁትንም ሦስት የተለያዩ ሥርዓቶችን ጠቅለል አድርጎ ለመገምገም ሲሞከር፥ መሠረታዊ የሆኑ ሀቆችን በሦስት ዓበይት የጊዜ ክልል ዙሪያ መድቦ ማየት ይቻላል። በእነኝህ የጊዜና የሥርዓት ክልሎች ያለፈውን ትውልድም ሆነ የራሷንም የሀገሪቱ የታሪክ ጉዞ ስንመለከት በየፈርጃቸው የሆኑቱን ሁኔታዎች ከሞላ ጎደል መገንዘብና መፈረጅ ከባድ አይሆንም።

በዚህ የጊዜና የሥርዓቶች ቀመር ስናይ፥ በመጀመሪያው ረድፍ ሊሰለፍ የሚችለው፥ ከ1933 እስከ 1966 ዓም ባለው ዘመን የነበረው ትውልድ ነው ማለት የሚቻል ይሆናል። የዚህ የዕድሜ ( ዘመን) ቀመር የሚጀምረው፥ ወራሪዋ ጠላት ኢጣሊያ፥ ከሀገራችን ከተባረረችበት ጀምሮ እስከ አፄው ሥርዓት ፍጻሜ ድረስ ያለውን ያጠቃልላል። ይህ ትውልድ በታሪክና በባህል ፥ በወግና በዕምነት፥ በሀገር ፍቅርና በጀግንነት አኳያ እየተማረ ያደገበት የራሱ የሆነ የኅብረተሰብ ዋጋና ክብር ነበረው። በአምስቱ የመከራ ዘመን ስለተከናወኑት የመስዋዕትና የጀግንነት፥ የሕዝብ ፍቅር፥ የሀገራዊ ስሜትና የአርበኞችን ገድልም በቂ ግንዛቤ ነበረው። ስለ ሰንደቅ ዓላማ ክብርና ሞገስ፥ ስለ ነፃነትና ስለ ሀገር ልዕልና ስለ ኢትዮጵያዊነት የመለያ ማንነትና ኩራት ብሎም ስለ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሕዝቦች የነፃነት ተምሰሌት መሆን፥ በማስረጃ የተደገፈ ትምሕርት እየተማረ ነበር ያደገው። የመማሪያ መጻሕፍቱና የሥርዓተ ትምህርቱ ዝግጅት የተመሰረተው በሁለንተናዊ ገፅታው፥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ሀገራዊ ማንነት ላይ ያተኮረ ነበር ለማለት ይቻላል። በዚያ ዘመን ትምሕርት ቤት የገባው ትውልድ፥ ካስተሳሰሩት ጠንካራ ሀብሎች መካከል፥ሥርዓተ-ትምሕርቱ፥የትምሕርቱ ጥራትና የመምሕራኑ ትጋት በመሆኑ፥ ሁሉም በአንድ አላማና ግብ ላይ ያተኩር ነበር። ይህም ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ ብሔራዊ ጥቅም ማሰብና መቆርቆር እንደነበር የሚካድ አይደለም። ከዚህም በቀር፥ያ ትውልድ በኩራትና በአርዓያ የሚያየው የአምስቱ ዓመት የጀግንነት ታሪክ አለኝታና የሚያደንቃቸው ሰማዕታት ጀግኖች ነበሩት። በአምስቱ የአርበኝነት ዓመታት ከባድ መስዋዕት በመከፈል ሀገሩን ከኢጣሊያ ወረራ ነፃ አውጥተው ያስረከቡትን አርበኞች ገድልና ጀግንነት እየተማረ አድጓል።

የኢትዮጵያ ጀግኖች፥ በብሄር፥ በሃይማኖት፥ በቋንቋና በክልል ሳይከፋፈሉ ለአንድ የጋራ ሀገራቸው መሰዋታቸው ተነግሮታል። ለዚህ አርዓያነት በግንባር ቀደም ሲጠቀሱለት የነበሩት፥ እነ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፥ በላይ ዘለቀ፥ ሁለቱ ወንድማማቾች፥ አበበና ደስታ ዳምጠው፥አሞራው ውብነህ፥ ኡመር ሰመተር፥ ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ፥ አብዲሳ አጋ፥ ዘረዓይ ድረስ፥ ሞገስ አስገዶምና አብረሃም ደቦጭ ፥ታከለ ወልደ ሐዋርያት፥ወይዘሮ አበበች ጨርቆስ፤ ወይዘሮ ልክ የለሽ በያን፤ወይዘሮ ከበደች ስዩምና ሌሎችም እልፍ ዕላፍ ሰማዕታት ሲሆኑ፥ በዲፕሎማቲክ መስክ ደግሞ ሎሬንሶ ታዕዛዝ፥ ብላቴን ጌታ ኤፍሬም ተወልደመድኅን፥ ፀሀፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድና ሌሎቹም በግንባር

ቀደም የሚጠቀሱ ይሆናሉ። ከዚህ አልፎ ተርፎ እንኳ፥ በስድሳዎቹ ዓመታት ከአውሮጳ ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ሀገሮቻቸውን ነፃ ለማውጣት የተጋደሉትን የአፍሪካን ጀግኖች ታሪክ፥ ማለትም፥ የክዋሜ ንክሩማህን፥ የጁሊየስ ኔሬሬን፥ የጆሞ ኬንያታን፤ የአህመድ ቤንቤላን፥ የፈራሃት አባስን፥ የሳሞራ ማሼልን፤ የአሚልካር ካብራልንና የመሳሰሉትን አፍሪካውያንን ገድል በጆሮው እየሰማ፥ በዓይኑ እያየ ያደገ ትውልድ ነበር። በዓለም አቀፍ ደረጃም ታላላቅ አብዮቶችና የነፃነት ትግሎች ድልን ሲቀዳጁ ለመመልከት በቅቷል። ይህም ክስተት በኋላ ጊዜ ላካሄደው አብዮታዊ ትግል ታሪካዊ አስተዋፅዖ አድርጎለታል።

በዚህ ዘመን ያደገው ትውልድ ይህንን ታሪክ የቀሰመው መጀመሪያ ከወላጆቹ ሲሆን፥ ቀጥሎም ከትምሕርት ቤት ስለነበር፥ ሀገሩን በዘመናዊ ሥልጣኔ ለመገንባትና የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለማስፍን ቆርጦ የተነሳበት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩት። አንደኛው፥ ከእርሱ በፊት የነበሩትን ጀግኖች ውለታ ለመክፍል አርአያቸውንም በመቀጠል ስለ አንዲቷ ታሪካዊትና ታላቂቷ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ማሰብ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከረሀብ፥ ከድንቁርና፥ ከድኅነት፥ ከበሽታ፥ከኋላ-ቀርነትና ከጭቆና አስተዳደር አላቅቆ፥ ፍትኅ-ርትዕ፥የሰፈነባትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የተረጋገጠባትና የተከበረባት ኢትዮጵያን ለመመስረት መታገል ነው። ይህንም ለውጥ ለማስገኘት፥ያ ትውልድ ከፍተኛ መሥዋዕት በመክፈል የባለውለታዎቹን አርበኞች ወረታ እንደሚከፍል ይሰማው ነበር። ታዲያ፥ ያ አብዮተኛ ትውልድ የሀገሩን ፍቅር የገለፀው፥ ከደርግ ጋር በመተናነቅ በከፈለው የአርበኝነት መስዋዕት ነበር ማለትይቻላል። ሀገርን መክዳትና ሕዝብን መበደልም ከቀደምት አርበኞችያልወረሰው ስለነበር፥የእነርሱን ዓርዓያ በተግባር ገልጾታል። እንደ ቀደምት አርበኛው ትውልድ ሁሉ፥እየኖረ ሞተ እንጅ፥ እየሞተ አልኖረም። ለሀገር-ለሕዝብ ጥቅምና ፍቅር ሲባል እየተጋደሉ መሰዋትን እንጅ፥ እየተዋረዱ መኖርን አልመረጠም። ውርደት የሚመጣው ደግሞ ከባዕድ ወራሪ ብቻ ሳይሆን ፥ ከሀገር ውስጥ ከሀዲ አምባገነኖችና ፀረ ሕዝብ መሪዎችም ጭምር በመሆኑ፥ የቀደምት አርበኞች የውጭ ወራሪ ኃይሎችን በመዋጋት አባርሮ እንዳስወጣቸው ሁሉ፥ እነርሱን የተካቸው ያ አብዮታዊ ትውልድም ከሃዲያን ሀገር ሻጮችንና ፀረ ሕዝብ መሪዎችን ተዋግቶ ማስወገድ የራሱ ትውልድ ድርሻና ግዴታ፥ ሀገራዊ ጥሪና ተልዕኮ መሆኑን በሚገባ ተረድቶና ታግሎም አኩሪ ታሪክን ፅፏል።ይህንንም አኩሪ ታሪክ በድጋሜ መጻፉ አይቀርም።

በደርግ ዘመን ተወልዶ ያደገው ትውልድ፥ ከርሱ ቀደም ብሎ ከነበረው ትውልድ የሚለይበት መሠረታዊ ሀቅ አለ። ወቅቱ የአብዮት ሂደት ስለነበረና የአብዮቱን ኢትዮጵያዊነት በነጠቁት ጥቂት ፋሽስታዊ መኮንኖች እጅ በመውደቁ ምክንያት፥ አዲሱ ትውልድ፥ ያገኘው ትምህርት፥ የኢትዮጵያን ታላቅነት ታሪካዊነት፥ የጀግኖቿን መስዋዕትነትና አርበኝነት ታሪክ ሳይሆን፥ አደኃሪነት፥ ኋላቀርነትን፥ ምድራዊ ሲዖልነት፥ የሚለውን ብቻ እየተጋተ እንዲያድግ ተደረገ፡፡ የሀገሩን አሉታዊ ገፅታ ብቻ እንጅ፥ አዎንታዊ ማንነቷን የሚገልፀውን ባኅርይና ማንነት ለማወቅ ተነፍጎት አደገ። በፋሽስታዊ ጭካኔ

በተካሄደው ጭፍጨፋና አረመኔያዊ  ግድያ ምክንያት ያ ጮርቃው አፍለኛ አዕምሮው ተመረዘ÷ ተሸማቀቀ ÷ ፍርሀትና መርበትበትን እየተማረ አደገ፡፡ ይህ ወጣት ትውልድ በራስ የመተማመንንና ሀገራዊ እሴትን÷ አሻፈረኝነትንና÷ ቆራጥነትን እንዳይላበሰ ተደረገ፡፡ በደርግ ድንፋታና የሀሰት ፕሮፓጋንዳ አዕምሮው እንዲደነዝዝ ሆን ተብሎ ዘመቻ ተካሄደበት፡፡ ቆራጥነትን መማር የሚቻለው  ከቆራጥ ጀግኖች እንጅ÷ ከጨካኝ አምባገነኖች ስለአልነበረ÷ ቆራጡ ኮሎኔል ሲባልለት የነበረው ጨካኝ ግለሰብ÷ በቆራጥነቱ ሳይሆን÷ ጭካኔ በተላበሰ ፍርሃቱ ሀገሪቱን ለክፉ ቀን አጋልጧት ኮበለለ፡፡ ጭካኔ ከፍርሀት እንጅ ከድፍረትና ከጀግንነት የሚመነጭ ባኅርይ ባለመሆኑ÷ ፈሪዎች ፍርሀትን ከማስተማር በቀር÷ ጀግንነትንም ስለማያስተምሩ÷ የደርግ የአስራ ሰባት ዓመታት የአሸባሪነት ሥርዓት÷ ሀገሪቱን ብቻ ሳይሆን÷ ትውልዱንም ጭምር አሁን ከአለበት ደረጃ እንዲወድቅ ምክንያት ሆነ፡፡
ይህ የዛሬው አሳረኛ ትውልድ በአጣብቂኝ ምርጫ ውስጥ እንዲወድቅ ተገዷል፡፡ እየኖሩ መሞት ወይም እየሞቱ መኖር!

ደርግን የተካውም የጠባብ ብሄረተኛ ድርጅት÷ ወደ ፖለቲካ መድረኩ ሲጠጋ ያገኘው÷ የደከመች ሀገርና መንፈሱ የተጎዳ ትውልድ ስለነበር÷ በባዶ ቤት ሰተት ብሎ ለመግባት ቻለ፡፡  ኢትዮጵያን ለማጥፋት  ያዘጋጀውን የተጠና አጀንዳ ለመተግበር ሁሉም ነገር ተመቻቸለት፡፡ የውጭ ባዕዳንንም ትብበር በሚገባ ተጠቀመበት፡፡ በስልትና በዕቅድ  በባዕዳን የተቀነባበረለትን አጀንዳውን ወይም ዕቅዱን ለማራመድም ብርቱ እንቅፋት አላጋጠመውም፡፡ ዕድሜ ለመንግሥቱ ኃይለማርያምና የወንጀሉ ተባባሪዎቹ÷ ከሞላ ጎደል እየኖረ የሚሞት ትውልድ እንጅ እየሞተ የሚኖር ትውልድ በብዛት አላጋጠመውም፡፡ ሀገር የምታበቅለው የዘራችውን እንጅ÷ ያልዘራችውን ማምረት ስለማትችል÷ በዚህ የደርግ ሰለባ ሆኖ ያደገው አዲስ ትውልድ የሚታዘንለት እንጅ የሚታዘንበት ሊሆን አይችልም፡፡ አይገባውምም፡፡

ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት በኢትዮጵያ ላይ የተዘረጋው ይህ ፀላዒ ሰናይት ዘረኛ አገዛዝ÷ በኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላው÷በዚህ የዛሬው ትውልድ ደግሞ በተለይ÷ተዘርዝሮ የማያልቅ የአጭርና የሩቅ አንደምታ ሊኖረው የሚችል በደልና ወንጀል ፈፅሞበታል፡፡ ይህ የዛሬው ትውልድ÷ ከእርሱ በፊት የነበረውን አብዮታዊ ትውልድ ጋሻ በማንሳት የሀገሩን ክብርና የሕዝቡን ነፃነት እንደሚያስከብር የታወቀ ቢሆንም÷ ከዚያ በፊት ግን እየሞቱ መኖርን እንጅ÷ እየኖሩ መሞትን እንደማይመርጥ የወያኔ መሪዎች ይፍጠንም ይቆይ ሊረዱት ይገባል፡፡ ያለውን ሁኔታ በግልፅ ስናቀርብም÷ በአንፃሩ መዘንጋት የሌሌለበት ሀቅ ደግሞ ይህ ትውልድ የተዘረጋበትን  የጠባቦች ወጥመድ እየበጣጠሰ በጋራ መታገልን መርጦ መስዋዕትነትን ለሀገሩም መክፈሉን ነው፡፡ የግንቦት 97ቱ ምርጫና የተከተለውም ትግል ለዚሁ ምሳሌ ሆኗል፡፡ አታጋይ ካገኘ÷ የኢትዮጵያ ወጣት የጥንት አርበኞችንና የፀረ ደርግ ታገዮችን ወኔ መውረሱን ለወያኔ ማሳየቱ አይቀርም፡፡ይህ ክስተት ደግሞ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ÷ የሕዝባዊ አመፁን ተላብሶ እንደሚመጣ የታሪክ ሀቅ ነው፡፡